
ህግህ ለእግሬ መብራት
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
ከዘፍጥረት - ዘዳግም
አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት
ክፍል አንድ
ከአድማሱ ተሾመ 1993 ዓ.ም

# ሕግህ ለእግሬ መብራት

ከአድነው ተሾመ

1993 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)

## ክፍል አንድ

ይህንን መጽሐፍ ያ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ
ወይም በከፊል ማባዛት ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው 1993 ዓ.ም

**Copyright 2001, Adnew Teshome**

# ምሥጋና

ከሁሉ በፊት፤ ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱ ለሆነው ለእግዚአብሔር ክብርና ምሥጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ። ይህንን ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያለውን የብሉይ ኪዳን ጥናት መጽሐፍ እንድጀምር፥ ጀምሬም እንድፈጽምና ለወገኖቼ እንዳቀርብ ስለረዳኝ እጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ።

ቀጥሎም፤ በዚህ ጥናት መጽሐፍ አስተዋጽዖ ያደረጉትን በሙሉ ማመስገን እፈልጋለሁ። አስቀድሜ፤ በሥጋም በመንፈስም ወንድሜ የሆነውን ቴዎድሮስ ተሾመን ሳላመሰግን አላልፍም። ወደ ጌታ ሙሉ ለሙሉ ከተመለሰ በኋላ ለእግዚአብሔር ቃል ትልቅ ረሃብና ጥማት ስለ ነበረው በእርሱ አነሳሽነት በጀመርነው የቤተሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው ይኼንን መጽሐፍ በዚህ መልኩ ለማዘጋጀት የቻልኩት። በተጨማሪም፥ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜያት በታማኝነት አብራ በመሳተፍ ያበረታታችኝን ውድ ባለቤቴን መድሎቴ ኃይሉን ጌታ ይባርክሽ ማለት እፈልጋለሁ።

መጽሐፉ በዚህ ከመቅረቡ በፊት፥ በአጻጻፉም ሆነ በይዘቱ በተሻሻለ መልክ እንዲቀርብ ረዥም ጊዜ በመውሰድ ጠቃሚ የሆኑ እርማቶችንና ገንቢ ሐሳቦችን የሰጡኝን ጋሽ ሰለሞን ከበደንና እትዬ ጥሩ ወርቅ መስፍንን ከልብ አመሰግናለሁ። በተጨማሪም፤ ጽሑፉን ተመልክተው ጠቃሚ ሐሳቦችን የሰጡኝንና ያበረታቱኝን ዶክተር ቶሎሳ ጉዲናን፣ መጋቢ አሳየኸኝ በርኼንና መጋቢ ዳንኤል አለማየሁን ከልብ አመሰግናለሁ።

ከሰው ስህተት አይጠፋምና፣ በዚህ የጥናት መጽሐፍ ውስጥ ላለው ለማንኛውም የአጻጻፍም ሆነ የአቀራረብ ስህተት ሙሉ ተጠ ያቂነቱን እኔ ስወስድ፥ አምሮና ጣፍጦ ለቀረበው ደግሞ በእግዚአብሔር ጸጋና ከላይ በጠቀስኳቸው ወገኖች አስተዋጽዖ እንደሆነ መጠቆም እወዳለሁ።

ይኼንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍ፣ የእግዚአብሔር ቃል ረሃብ ላላቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ማበርከት እፈልጋለሁ። በተለይ አብዛዎኛቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት የሚገኙት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለ ሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማይችሉ እና ቋንቋውን ቢችሉም እነዚህን መጻሕፍት ማግኘት የማይችሉ ወገኖቻችን በቃሉ ውስጥ ያለውን በረከት በጥቂቱም ቢሆን ከዚህ መጽሐፍ እንዲያገኙ ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

ይኼንን የጥናት መጽሐፍ፤ ለግል ወይም ለኅብረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጠቀም ይቻላል።

# ማውጫ

መቅድም ........................................................................ 6

መግቢያ ........................................................................ 8

ምዕራፍ አንድ

የእግዚአብሔር ቃል ........................................................10

ምዕራፍ ሁለት

ኦሪት ዘፍጥረት ............................................................. 24

ምዕራፍ ሦስት

ኦሪት ዘጸአት ............................................... .............. 41

ምዕራፍ አራት

ኦሪት ዘሌዋውያን........................................................... 67

ምዕራፍ አምስት

ኦሪት ዘኍልቍ............................................................ 107

ምዕራፍ ስድስት

ኦሪት ዘዳግም ............................................................ 157

# መቅድም

መጽሐፍ ቅዱስ በአማኝ ሊወደድ፥ ተዘውትሮም ሊነበብ፥ አንባቢውም ተረድቶት ሊኖርበት የሚገባ በአምላካችን በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠን መጽሐፍ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክቶች አንባብያን በሚገባ እንዲረዱት የሚያግዙ መጽሐፎች የአንባቢውን ጊዜ በመቆጠብ የመልእክቱን ደራሽነት በማጎልበት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ይህም መጽሐፍ በጠባዩ ከዚሁ ጎራ የሚመደብ ነው። አቶ አድነው ተሾመ በዚህ ረገድ «ጎሽ» የሚያሰኝ ጠ ቃሚ ሥራ አዘጋጅተው እነሆ ብለውናል። እንዲህ እጥር ምጥን ባለ መልክ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ገጽታ መሠረታዊ ሐሳቦችን ያነሣና ባገር ቋንቋ የተጻፈ ዓይነተኛና እንደ እኔ የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው።

ይህ መጽሐፍ በጥድፊያ የሚነበብ መጽሐፍ አይደለም። ጸሐፊው ያነሱአቸው ርእሰ ጉዳዮች ጸጥታንና ልብታን የሚሹ ናቸው። የተነሡትን ርእሰ ጉዳዮች በጥሞና ያውጠነጠነ አንባቢ ብዙ ጠቃሚ እውቀት ያገኝበታል።

መጽሐፉ በስድስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን፥ የመጀመሪያው ምዕራፍ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት እንደ ተጻፉ በማን እንደ ተጻፉ፥ አሁን ባሉበት ሁኔታ እንዴት እንደ ተገኙ ባጭር ባጭሩ ይነግረናል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክቶ ወደ አሥራ ሁለት የሚጠጉ ሐሳቦች ተነሥተዋል። ከዚህ በኋላ ያሉት አምስት ምዕራፎች የሚያተኩሩት በአምስቱ የሙሴ ሕግ መጻሕፍት ላይ ሲሆን፥ የየመጻሕፍቱ ዐቢይ ሐሳብ ከዝርዝር ትንታኔው ጋር ቀርቦአል።

ጸሐፊው የየመጻሕፍቱን ዋና ዋና ትምህርት (ጭብጥ) ፈልፍለውና ፈልቅቀው ከማቅረባቸው በላይ ከየመጻሕፍቱ ልንማራቸውና ከዕለት ተዕለት ኑሮአችን ጋር ልናዛምዳቸው የሚገቡ ቁም ነገሮችን ቅቡል በሆነ መልክ አቅርበውልናል። ይህ አንዱ የመጽሐፉ ጠንካራ ጎን ነው። አንድ ጸሐፊ ይህ ማለት እንዲህ ነው» ብሎ በዚያው ከተወን፥ የሠራው ግማሽ ሥራ ብቻ ይሆናል። ነገር ግን፥ «ይህ የሚያመለክተው ይህን ነው» ካለን በኋላ በዚህ መነሻነት ይህን እንማራለን፤ እንግዲያስ በአካሄዳችን በአስተሳሰባችን እንዲህ ሆኖ መገኘት ይጠበቅብናል ካለን እንኪያስ ሥራው ተሟልቷል ማለት ነው።

ጸሐፊው ስለ እስራኤላውያን ሕይወትና ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ነበራቸው ግንኙነት ብቻ ሲነግሩን አልዋሉም፤ እግዚአብሔር ከእኛ ምን እንደሚጠብቅና በፊቱም እንዴት መገኘት እንዳለብን የቃሉን እውነት በመመርኮዝ ነግረውናል። በሌላ አነጋገር ጸሐፊው ወደ ጥንት እስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ ዶለውን (ጨምረውን) እንደ ፍጥርጥራችሁ ብለው እዚያው አልተዉንም። ይልቁንም፥ በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ ራሳችንን እንድናይና እንድንመረምር ረድተውናል። አንባቢዎች ካነበቡት ነገር ሊገነዘቡትና ከሕይወታቸው ጋር ሊያዛምዱት የሚገባውን እውነት ፍንትው አድርጎ ያሳየ ጽሑፍ ነው (በገጽ 124 ላይ ያሉት ጥያቄዎች ለአብነት ይመለከቷል)።

በሌላ በኩል ደግሞ በእያንዳንዱ ምዕራፍ መዝጊያ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች፥ አንብበን ካለፍነው ምዕራፍ ውስጥ ምን ያህል ቁም ነገሮችን እንደ ጨበጥን ይፈትሹናል። ይህም የመጽሐፉ ሌላው በጎ ጎን ነው። ጥያቄዎቹ ያነበብነውን ምዕራፍ እንድንከልስ ከማስቻላቸው በላይ፥ «ከዚህ ነገር ምን እማራለሁ? እግዚአብሔር ከእኔ ምን ይፈልጋል?» እያልን ራሳችንን እንድንጠይቅ ያዘጋጁናል፤ ለለውጥ እርምጃም ያነሣሡናል።

በመጨረሻም፥ ጸሐፊው በማጣቀሻነት የተጠቀሙባቸው መጻሕፍት በብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ ተነባቢነት ያላቸው መጻሕፍት በመሆናቸው፥ ለመጽሐፉ ይዘት ጥንካሬና ተአማኒነት ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ሰለሞን ከበደ

# መግቢያ

አንድ ክርስቲያን ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል (መጽሐፍ ቅዱስን) የበለጠ በተረዳ መጠን የእግዚአብሔርን ፈቃድና እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያለውን ዘላለማዊ ዓላማ የበለጠ ስለሚረዳ በሕይወት ዘመኑ የእግዚአብሔርን አሳብ ለማገልገልና ለመፈጸም ዝግጁ ይሆናል፡፡ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቃል የነበረውን ፍቅርና አክብሮት ለመረዳት መዝሙር 119ኙን ብቻ ማንበብ ይበቃል፡፡ በሕይወት ዘመኑ የራሱን አሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን አሳብ ማገልገል የቻለውም የእግዚአብሔርን አሳብ ከእግዚአብሔር ቃል በደንብ ተረድቶ ስለ ነበረ ነው፡፡ «ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ» (ሐዋ. 13፥36)፡፡

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ጥናት ተጸንሶ የተወለደውም የእግዚአብሔርን ቃል ሥርዓት ባለው መልክ ለማጥናት ከነበረኝ ምኞት የተነሣ ነው፡፡ «ጌታ ሆይ፥ እባክህ ቃልህን በደንብ መማር እንድችል ለሁለት ዓመት እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ እንድማር ሁኔታዎችን አመቻችልኝ» በማለት ረዘም ላለ ጊዜ ጌታን እለምን ነበረ፡፡ መቼም እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚመልስበት መንገድ የተለያየ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እኛ በጠበቅነው መንገድ አይመጣም፤ ውጤቱ ግን እንደለመንነው ወይም ከለማነው በላይ ይሆናል፡፡ ይኼንን ጸሎት በምጸልይበት ጊዜያት መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ መጻሕፍትን አገኘሁ፡፡ መቼም አንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ቢገባም አስተማሪው መመሪያ የሚሆኑ መጻሕፍትን በመከተል የሚያስተምረውን ትምህርት ነው የሚማረው፡፡ እነዚህ መመሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ከተገኙ ራስንም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ማስተማር ይቻላል ማለት ነው፡፡ እነዚህን መመሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን ከጥቂት ወገኖች ጋር ማጥናትና ማስጠናት ጀመርኩ፡፡ ይህ ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያለው ክፍል ብቻ ከአንድ ዓመት በላይ የፈጀብን ጥናት ነው፡፡

ከላይ እንደ ጠቀስኩት ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ጥናት በተለያዩ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት በሚረዱ መጻሕፍት እርዳታ ስናካሄደው ከነበረው ጥናት የመነጨ ስለሆነ በዚህ ጥናት ውስጥ ላለው ለአብዛኛው ቁም ነገር ምሥጋናውን እነዚህን መጻሕፍት ለደረሱ የእግዚአብሔር ሰዎች እሰጣለሁ፡፡ በተለይ በ Dr,

J, Sidlow Baxter የተጻፈው "EXPLORE THE BOOK" የሚለው መጽሐፍ ለዚህ ጥናት እንደ ጀርባ አጥንት የተጠቀምንበት መጽሐፍ ነው። እኚህ የእግዚአብሔር ሰው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስላበረከቱት ስጦታ ጌታ ይባርካቸው ማለት እፈልጋለሁ። ይህንንም ስል ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ጥናት የዚህ መጽሐፍ ግልባጭ ነው ማለትም አይደለም። ከሌሎችም መጻሕፍትና ከግል ጥናት የተውጣጣ ነው።

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላና <u>የነገርን ሁሉ ስር</u> የያዘ እንደመሆኑ መጠን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ መሠረታዊ የሆኑ መንፈሳዊ ትምህርቶች እንደሚገኙ መዘንጋት የለብንም። ብሉይ ኪዳንን በቅጡ ሳይረዱ የአዲስ ኪዳንን መልእክት ሙሉ ለሙሉ መረዳት አስቸጋሪ ነው። ጳውሎስ በሮሜ 15÷4 «... የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጻፈ» ሲል፣ የብሉይ ኪዳንን አስፈላጊነት በማስገንዘብ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ጠቃሚ ትምህርቶች እንድንማር ሊያነቃቃን ነው።

ምዕራፍ አንድ÷ በአጠቃላይ ስለ እግዚአብሔር ቃል ባህርይ÷ አመጣጥና አስተማማኝነት የሚናገር ሲሆን፣ ከምዕራፍ ሁለት እስከ ስድስት ያሉት ምዕራፎች ደግሞ ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉት ምዕራፎች የሚገልጹ ናቸው።

አድነው ተሾመ

ምዕራፍ አንድ

# የእግዚአብሔር ቃል

## ፩ የእግዚአብሔር ቃል ባህሪያት

.<u>ሕያውና የሚሠራ ነው</u>

«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፡፡ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ. 4÷12)፡፡

.<u>መንፈስና ሕይወት ነው</u>

«... እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው፡፡» (ዮሐ. 6÷63)

.<u>ተልዕኮውን የሚፈጽም ነው</u>

«ዝናብን በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ÷ ምድርን እንደሚያረካት፣ ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም፡፡» (ኢሳ. 55÷10-11)

.<u>እንደ እሳት የሚያጠራና ገላባውን የሚያቃጥል</u>

.<u>እንደ መዶሻ ደግሞ ጠንካራውን ልብ የሚሰብር ነው</u>

«በውኑ ቃሌ እንደ እሳት ድንጋዩንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደለችምን?» (ኤር. 23÷29)

.<u>ተንኮል የሌለበት ንጹህ ቃል ነው</u>

«... በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ» (1ጴጥ. 2÷3)፡፡

«በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃላት <u>የነጹ ቃላት ናቸው</u>» መዝ. 11÷(12)÷6)፡፡

.<u>ጣፋጭ ነው</u>

«ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ» መዝ. 119፥103፡፡

.<u>ምሪትን የሚሰጥ ብርሃን ነው</u>

«ሕግህ ለእግሬ <u>መብራት</u> ለመንገዴ <u>ብርሃን</u> ነው» (መዝ. 119፥105)፡፡

<u>በምክርና በዕውቀት የተሞላ ነው</u>

«የእውነትን ቃል እርግጥነት አስታውቅህ ዘንድ፣ ለሚጠይቅህም እውነትን ቃል መመለስ ይቻልህ ዘንድ በምክርና በዕውቀት የከበረን ነገር አልጻፍሁልህምን?» (ምሳ.22፥20-21)

## ፪. የመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል

መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻሕፍትን ያዘለ ነው፡፡ ብሉይ ኪዳንና አዲስ በመባል ይከፈላል፡፡

ብሉይ ኪዳን -39 መጻሕፍት፤ አዲስ ኪዳን -27 መጻሕፍት

ሀ. <u>ብሉይ ኪዳን</u> - 17 የታሪክ መጻሕፍት
5 የቅኔ መጻሕፍት
17 የትንቢት መጻሕፍት አሉት

<table>
<tr><td colspan="2">17 የታሪክ</td><td></td><td>5የቅኔ</td><td colspan="3">17 የትንቢት</td></tr>
<tr><td rowspan="2">5 የህግ</td><td rowspan="2">9 በተስፋይቱ ምድር</td><td rowspan="2">3 በስደት</td><td rowspan="3">ኢዮብ<br>መዝሙረ ዳዊት<br>ምሳሌ<br>መክብብ<br>መኃልይ</td><td>5 ታላላቅ ነቢያት</td><td colspan="2">12 ታናናሽ ነቢያት</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ኢሳይያስ<br>ኤርምያስ<br>ሰቆቃወ<br>ሕዝቅኤል<br>ዳንኤል</td><td>9 ከስደት በፊት</td><td>3 ከስደት በኋላ</td></tr>
<tr><td>ከዘፍጥረት<br>↓<br>ዘዳግም</td><td>ከኢያሱ<br>↓<br>2ዜና</td><td>እዝራ<br>ነህምያ<br>አስቴር</td><td>ከሆሴዕ<br>↓<br>ሶፎንያስ</td><td>ሐጌ<br>ዘካርያስ<br>ሚልክያስ</td></tr>
</table>

አምስቱ የቅኔ መጻሕፍት የግለሰብ ልምምዶች ናቸው፡፡

ኢሳይያስና ኤርምያስ- ከስደት በፊት፤ ሕዝቅኤልና ዳንኤል-በስደት ጊዜ

ለ. አዲስ ኪዳን -5 የታሪክ፥ 21 መልእክቶች፥
1 የትንቢት መጻሕፍት ያዘለ ነው።

## ፫. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዘመን

ብሉይ ኪዳን - ከ1400B.C – 400 B.C
(ከሙሴ እስከ ሚልክያስ)
አዲስ ኪዳን -ከ33 A.d - 100 A.d
በአጠቃላይ - ከ1400B.C – 100 A.d
በ1500 ዓመታት ውስጥ ተጻፈ

## ፬. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው ቋንቋዎች

ብሉይ ኪዳን -ዕብራይስጥ (አብዛኛው)
[1]አረማይክ- ጥቂት- የዳንኤልና የዕዝራ ክፍሎች
አዲስ ኪዳን-ግሪክ

## ፭. የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ መልዕክት

«በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚገኘው ደኅንነት»

«በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3፥16)።

## ፮. የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ግለሰብ- ኢየሱስ ክርስቶስ

«እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፣ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው» (ዮሐ. 5፥39፤ ቆላ. 2፥16-17)። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩ ጥቂት ተጨማሪ ጥቅሶች፤ ዘፍ. 3፥15፤ ኢሳ. 7፥14፤ 9፥6፤ ኢሳ 53፤ መዝ. 22:1፤ 16-18፤ መዝ. 2፥
«ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው» (ሉቃ. 24፥27)።
ብሉይ ኪዳን «ዓለምን የሚያድነው መሲሕ ይመጣል» ሲል፤ አዲስ ኪዳን ደግሞ «መሲሑ መጥቷል» ይላል።

ብሉይ ኪዳን ⟶ ኢየሱስ ✝ ክርስቶስ ⟵ አዲስ ኪዳን

## ፯. የመጽሐፍ ቅዱስ አመጣጥ

በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ - 2ጴጥ. 1÷20-21፤ 2ጢሞ. 3÷15-16
1ቆሮ. 11÷23፤ 1ተሰ. 2÷13፤ ገላ. 1÷11-12
«የተናገርኩህን ቃል ሁሉ ጻፍበት» ኤር. 36÷2




–እግዚአብሔር ቃሉን ሰጠ፣ የእግዚአብሔር ሰዎች ቃሉን ተቀብለው ጻፉት ወይም ተናገሩት።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ደጋግመው የሚናገሩት ቃል፤ «የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ» የሚል ነበረ።

## ፰. የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ግብ

-ሁሉን በክርስቶስ ኢየሱስ ለመጠቅለል (ኤፌ. 1÷10)
«ኃጢአት የሌለበት ምልዓተ ዓለም»
ራእ. 21÷1-18፤ 22÷1-5፤ ኢሳ. 33÷17-22

## ፱. የመጽሐፍ ቅዱስ አሰባሰብ

የእግዚአብሔር ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት ለማካተት የተጠቀሙባቸው መመሪያዎች[2]።

1. ከእግዚአብሔር የሆነ መንፈሳዊ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ነው?

2. ትንቢታዊ ነው?
3. እውነተኛ ነው ወይስ ተረት ተረት?
4. ሕይወትን የመለወጥ ኃይል አለው?
5. በዘመናት በነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ተቀባይነት ነበረው ወይ?
   በ2ጴጥ. 3፥16 ጴጥሮስ የጳውሎስን ጽሑፍ ሲቀበል እናያለን፡፡
6. ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ጋራ ይስማማል ወይ?

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከላይ ከተጻፉት መመሪያዎች በተጨማሪ፣ የተጻፉት በሐዋርያት ወይም በሐዋርያት ሥልጣን /Apostolic Authority/ መሆኑ ይረጋገጥ ነበረ፡፡[3] (ኤፌ.2፥20፣ ሐዋ.2፥42)

ከ 66ቱ መጻሕፍት ውጭ የሆኑት መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተካተቱበት ምክንያት ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ስለማያልፉ ነው፡፡ ለምሳሌ፥ ከሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት አንዱ በሆነው በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ፣ «እነሱንም ፀንሰው ረጃጅሞች አርበኞች ልጆችን ወለዱ፣ ቁመታቸውም ሦስት ሦስት ሺህ ክንድ ነው» (መጽሐፈ ሄኖክ 2፥12)፡፡

- በተጨማሪም፥ እነዚህ ልጆች፣ «ከደመና የሚደርሱ ረጃጅሞች ሰዎች» እንደነበሩ በዚሁ መጽሐፍ በምዕራፍ 4 ቁ. 85 ተጠቅሷል፡፡ ይህ ታሪክ ከላይ በተራ ቁ.3 የተገለጸውን መሥፈርት ያሟላ እንደሆነ አንባቢው ይፍረደው፡፡ ብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ የተሰጠው ለእስራኤላውያን እንደመሆኑ መጠን እስራኤላውያን በታሪክም ሆነ በዘመናችን ቅዱሳት መጻሕፍት ብለው የተቀበሏቸው 39ኙን መጻሕፍት ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም፥ በአዲስ ኪዳን በወንጌልና በሐዋርያት መልዕክቶች ውስጥ ኢየሱስና ሐዋርያቶች ከአብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም፥ በአዲስ ኪዳን በወንጌልና በሐዋርያት መልዕክቶች ውስጥ ኢየሱስና ሐዋርያቶች ከአብዛኛውዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዙ ጥቅሶችን ሲጠቅሱ ተጨማሪ ከሆኑት መጻሕፍት ግን ምንም ሲጠቀሱ አናይም፡፡ በይሁዳ መልዕክት ብቻ፣ ሄኖክ ጌታ ጳግም ምጽአት ትንቢት እንደተናገረ ተጽፏል፡፡ ሆኖም ከሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት አንዱ የሆነው መጽሐፍ ሄኖክ ከላይ የተገለጹትን መሥፈርቶች እንደማያሟላ መጽሐፉን በጥሞና ላነበበው ሁሉ ግልጽ ነው፡፡

፲. መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደርጉት ነገሮች፡፡

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት 66 መጻሕፍት፣

- በ1500 ዘመናት ተጻፉ
- በ40 ያህል <u>በተለየየ ደረጃና ሁኔታ ባሉ ሰዎች</u> ተጻፉ

- በነገሥታት፣ በእረኞች፣ በዓሣ አጥማጆች፣ በጦር መሪዎች በሐኪም (ሉቃስ)፣ በምሁር (ጳውሎስ)፣ በፈላስፋ ሰሎሞን፣ በጠቅላይ ሚኒስቴር (ዳንኤል) ወዘተ…
- <u>በተለያዩ አህጉሮች</u> በአፍሪካ፣ በእስያና በአውሮጠ

<u>በተለያዩ ቦታዎች</u>፣ በበረሃ፣ በእስር ቤት፣ በቤተ መንግሥት፣ በሜዳ (በእረኝነት)፣ በደሴት ላይ ዮሐ. ራእ ወዘተ…

<u>በተለያዩ የስሜት ዓይነቶች</u>: - በደስታ፣ በኀዘን፣ በሰቆቃ በሥቃይ፣ በፍቅር፣ ግራ በመጋባት፣ በመፈላሰፍ ወዘተ…

<u>በሦስት ቋንቋዎች</u>: - ዕብራይስጥ፣ አረማይክ፣ ግሪክ

በተለያዩ ሰዎች፣ ሁኔታዎችና ዘመናት የተጻፉ ቢሆንም መልዕክታቸው የተያየዘ፥ አንድ ወጥ የሆነና ወደ አንድ አቅጣጫ የሚያመራ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ያደርገዋል።

2. የተለያዩ ዓይነት ስደቶችን ያለፈ መጽሐፍ ነው።

ሀ. ብዙ፤ መጽሐፍ ቅዱስን የማጥፋት ዘመቻን አሸንፎአል

- 5 ቮልቴር የሚባለው የፈረንሳይ ፈላስፋ በ100 ዓመታት ውስጥ ክርስቲያኖችና መጽሐፍ ቅዱስ ይጠፋሉ ብሎ ነበር። ነገር ግን በሞተ በ50 ዓመቱ (እ.ኤ.አ በ1828 ዓ.ም.) የእርሱ ቤትና ማተሚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማተሚያ ቤት ሆነ። ሊቀብሩት ያሰቡትን በመቃብራቸው ላይ እያበበ የሄደ መጽሐፍ ነው።
- [6]ዳዮክሊሽያን የሚባል ንጉሥ (303 A.D) መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ እንዲቃጠል አዋጅ አስነግሮ ነበር። ነገር ግን ከ 25 ከ25 ዓመታት በኋላ ኮንስታንቲን የሚባለው ተከታዩ ንጉሥ 50 መጽሐፍ ቅዱሶች በመንግሥት ወጪ እንዲዘጋጁ ትእዛዝ ሰጠ።

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን መልእክት የተቃውሞ ዘመቻ ንባባዊ ዊ-ስ /Textual Criticism/

- 7 በሙሴ ዘመን መጻፍ በደንብ ስላልተጀመረ ሙሴ የመጀመሪያዎቹን አምስት መጽሐፍት ሊጽፍ አይችልም ተብሎ ነበር። ነገር ግን በሥነ-ቅርስ ጥናት (አርኪዎሎጂ) የተገኘ ማረጋገጫ እንደሚያሳየው ከሙሴ በፊት (በሐሙራቢ) ዘመን በነበሩት ዘመናት እንኳን የጽሑፍ ችሎታ እንደ ነበረ ተረጋግጦአል።
- በተጨማሪ ብዙ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የመጡ ተቃውሞዎች በሥነ-ቅርስ ጥናት ግኝቶች ፈራርሰዋል።

3. በመጀመሪያ በማተሚያ የታተመ መጽሐፍ ነው (1455 A.D)
4. ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ በላይ በብዙ ቋንቋዎች የተተረጎመ መጽሐፍ ነው።
5. ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ በላይ በብዛት የታተመና አሁንም የሚታተም መጽሐፍ ነው።

6. በመጀመሪያ ከተጻፈበት ቋንቋ በሌላ ቋንቋ ለመጀመሪያ የተተረጎመ መጽሐፍ ነው::
7. በሳይንስ በቅርብ የታወቁ እውነቶችን ከ2000 ዓመታት በላይ ይዞ የኖረ መጽሐፍ ነው::
- የመሬት ክብ መሆን -ኢሳ. 40፥22
- ምድር ያለ ድጋፍ መንሳፈፍ - ኢዮብ 26፥7
- የዝናብ አዘናነብ ሂደት- መክ. 11፥31፤ ኢዮ. 36፥27-28፤ ኢዮ. 37፥11፤ ኢዮ. 38፥28-30
- የብርሃን አከፋፈል (በጥያቄ መልክ) -ኢዮብ 38፥24 (ቀስተ ደመና የሚሆነው ብርሃን ሲከፋፈል እንደሆነ በሳይንስ ተረጋግጧል)
- ሥጋ አፈር እንደሆነ፤ (ዘፍ. 2፥7፤ 3፥19-) በሰው ሰውነት ውስጥ ያለው ንጥረ ነገር በሙሉ በአፈር ውስጥ እንደሚገኝ በሳይንስ የታወቀው በቅርብ ጊዜ ነው::
- በተጨማሪ፤ በኢዮብ 38-40 ከሰው አእምሮ በላይ የሆኑትን ጥያቄዎች እግዚአብሔር ኢዮብን ሲጠይቀው እናያለን::

8. ከሁሉ በላይ፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጥሩ ሰዎችን ሕይወት የለወጠ ነው::

## ፲፩. የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማማኝነት

<u>1. የመጽሐፉ በጥንቃቄ የመገልበጥና የመያዝ ሁኔታ</u>: -

<u>አዲስ ኪዳን</u>: - [8]ካሉት የዓለም መጻሕፍት ሁሉ እንደ አዲስ ኪዳን ብዙ ቅጂዎች (Manuscripts) ያሉት መጻሕፍት የለም:: ከ5,300 በላይ የግሪክ፤ ከ10,000 በላይ የላቲን፤ እንዲሁም ከ 9,300 ያላነሱ የሌሎች ቋንቋዎች ቅጂዎች አሉት:: በተጨማሪ፥ ከ24,000 በላይ የአዲስ ኪዳን ንዑስ ክፍሎች ቅጂ አሉት:: ከአዲስ ኪዳን ጋር የሚወዳደረው ሁለተኛው መጽሐፍ የሆሜር ኢሊያድ ሲሆን፣ እርሱም 643 ቅናዎች አሉት::

| መጻሕፍት | የተጻፉበት ጊዜ | የመጨረሻው ቅጂ ዘመን | የጊዜ ልዩነት |
|---|---|---|---|
| ብሉይ ኪዳን ከሙት ባህር የተገኙ (Dead Sea Scrolls) | 1400-400 B.C | 100 B.C | 300 ዓመታት |
| አዲስ ኪዳን | 40-100 A.D. | 125 A.D. | 25 ዓመታት |
| ኢሊያድ (ሆሜር) | 900 B.C | 400 B.C | 500 ዓመታት |

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው እነዚህ የአዲስ ኪዳን ቅጂዎች ከመጀመሪያው ከዋናው መጽሐፍ ጋር የሚለያዩት በ25 ዓመታት ብቻ ነው ከ (100 A.D. እስከ 125 A.D) በዓለም በጣም አስተማማኝ የሚባለው የሆሜር ኢሊያድን ግን በመጀመሪያውና በቅጂው መካከል የ500 ዓመታት ልዩነት አለ፡፡

ብሉይ ኪዳን - ከሙት ባህር (Dead Sea scrolls) ከተገኙት ቅጂዎች በፊት የነበረው የብሉይ ኪዳን ግልባጭ በ900 A.D የተገለበጠ ነበረ፡፡ ብሉይ ኪዳን ተጽፎ ያለቀው በ400 B.C ስለሆነ የ1300 ዓመታት ልዩነት ነበረ ማለት ነው፡፡ ከሙት ባህር የተገኙት የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች ሲመረመሩ ግን ተጻፉ ተብሎ የሚገመተው በ100 B.C ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ከ400 B.C እስከ 100 B.C - የ300 ዓመታት ልዩነት ብቻ እንዳለ ማየት እንችላለን፡፡

<u>ከሙት ባህር የተገኙት ጽሑፎች</u>

በአጠቃላይ 40,000 የሚሆኑ ጽሑፎች ተገኝተዋል፡፡[9]

- ከእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ 500 የሚሆኑ መጻሕፍት ሊገኙ ችለዋል፡፡
- ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሌላ ብዙ መጻሕፍት ተገኝተዋል፡፡
- የኢሳያስ መጽሐፍ በከፊል ሳይሆን በሙሉ ይገኝበታል፡፡

<u>እንዴት ተገኙ?</u> በመጋባት 1947 (እ.ኤ.አ) (March 1947) አንድ የጠለስታይን እረኛ የሆነ ሙሐመድ የሚባል ልጅ አንዲት ፍየል ጠፍታበት በሙት ባህር ምዕራብ በኩል ወደሚገኝ ገደላማ ሥፍራ ድንጋይ ይወረውራል የወረወረው ድንጋይ በአንድ ዋሻ ውስጥ አንድ ማሰሮ ሲሰብር ይሰማል፡፡ ምንድነው? ብሎ ወደዚህ ዋሻ ሄዶ ሲያይ ብዙ ትላልቅ ማሰሮች ያያል፡፡ እነዚህ ማሰሮዎች የብራና ጥቅሎች የያዙ ሆነው በጨርቅ የተሸፈኑ ነበሩ፡፡ እነዚህ ማሰሮዎች አፋቸው በደንብ የተደፈነ ነበረ፡፡ እነዚህ ማሰሮዎች ለ1900 ዓመታት ያህል በእንደዚህ ሁኔታ እንደተጠበቁ ይታመናል ምክንያቱም እዚያ ቦታ በእንደዚህ ሁኔታ ተቀመጡ ተብሎ የሚታመነው በ68 A.D ነው፡፡

ከእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ ሙሉ የኢሳይያስ መጽሐፍ ተገኝቷል፡፡ ይኼ የኢሳይያስ መጽሐፍ ቅጂ በ125 B.C የተጻፈ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡ ይኼኛውን የኢሳይያስ መጽሐፍና ከዚያ በፊት ይጠቀሙበት የነበረውን በ916 A.D የተባለውን ግልባጭ ሲያወዳድሩ በ1041 ዓመታት የተለያዩ ቅጂዎች ቢሆኑም አንድነታቸው በጣም

የሚያስገርም ነው። ከጥቂት የሆሄያት ልዩነት በስተቀር የመልዕክቱን ይዘት የሚለውጥ ምንም ዓይነት ልዩነት የላቸውም።

## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዴት ይገለበጡ ነበር?

በድሮ ዘመን ጽሑፎች የሚጻፉባቸው ነገሮች ብዙ የሚቆዩ ስላልነበሩ በየጊዜው ወደ ሌላ መጻፊያ መገልበጥ ነበረባቸው። በተለይ በእስራኤላውያን መካከል ዋና ሥራቸው ብሉይ ኪዳንን መገልበጥና መጠበቅ የሆነ ሰዎች (ጸሐፍት) ነበሩ። ይህንንም የመገልበጥ ሥራ በሚያስደንቅ ጥንቀቄና ያከናውኑ ነበር።

ከሚወስዷቸው ጥንቃቄዎች ውስጥ: - [11]

ሀ. የሚገለበጡት መጻሕፍት ውስጥ ያሉት የቃላትና የሆሄያት ብዛት ይቆጠራል።

ለ. በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የመካከለኛዋ ቃልና ፊደል ምን እንደ ሆነች ይታወቃል።

ሐ. በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዷ ፊደል ስንት ጊዜ እንደ ተጻፈች ይታወቃል።

መ. የአምስቱ የሙሴ የመጻሕፍት (ኦሪት) መሐከለኛ ቃልና ፊደል ይታወቃል።

ሠ. የብሉይ ኪዳን በሙሉ መሐከለኛ ቃልና ፊደል ይታወቃል። በአጠ ቃላይ፤ «ሊቆጠር የሚችለው ነገር ሁሉ ይቆጠራል»

ይህ ሁሉ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸውን አክብሮትና የእግዚአብሔር ቃል በምን ዓይነት ጥንቃቄ ተጠብቆ እንደኖረ ያሳያል።

2. <u>የሥነ-ቅርስ ጥናትና ምርምር ማረጋገጫ</u>

ሌላው፤ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተማማኝነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሥነ-ቅርስ ጥናት ነው። ይህም፣ በድሮ ዘመን ተቀብረው የነበሩትን ታሪኮችና ባህሎች ከምድር ቆፍሮ በማውጣት የሚደረግ ምርመራና ጥናት ነው። ብዙ ትክክል አይደሉም የተባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና ሁኔታዎች በሥነ-ቅርስ ጥናት ሲደገፉ እናያለን።

ሀ. በሙሴ ዘመን ጽሑፍ ስላልነበረ ሙሴ ኦሪትን ሊጽፍ አይችልም ይባል ነበረ፤ ነገር ግን በሥነ-ቅርስ ጥናት የተገኘ ማስረጃ ከሙሴ በፊት በነበረ ሥልጣኔ እንኳን የጽሑፍ ችሎታ እንደ ነበረ ያስረዳል:: ይህም፣ ኢብላ (Ebla) ትባል በነበረ ከተማ (2300 B.C) በአሁኑ በሰሜን ሶርያ በሚገኝ ሥፍራ፣ የተገኙ ጽሑፎች ከሙሴ (1400 B.C) 900 ዓመታት በፊት እንኳን የጽሑፍ ችሎታ እንደ ነበራቸው ያረጋግጣል:: [12]

ለ. በዘፍ. 14 ላይ አብርሃም የአምስቱን ከተሞች ነገሥታት መዋጋቱና ድል ማድረጉ በብዙ ምሑራን አስተማማኝ አልነበረም:: ነገር ግን፤ በዚችው ከተማ (ኢብላ-Ebla) የተገኘው ማስረጃ በዘፍ. 14 ያሉትን ከተሞች በቅድም ተከተል ይጠቅሳቸዋል:: ከዚህ ግኝት በፊት የእነዚህ አምስት ከተሞች መኖር እንኳን እውነት አይደለም በማለት የሚቃወሙ ምሑራን ነበሩ::

ሐ. ሉቃስ በወንጌሉ (ሉቃ. 2÷1-3) በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ዘመን የሕዝብ ቆጠራ ነበረ የሚለው ውሸት ነው ሕዝቡም ሲቆጠሩ «ወደ ትውልድ አገራችሁ ተመለሱ» አይባሉም ነበረ፤ ቄሬኔዎስ ደግሞ በዚያን ጊዜ አገረ ገዥ አልነበረም የሚሉ ተቺዎች ነበሩ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ ትክክል መሆናቸው በሥነ-ጥናትና በታሪክ የተረጋገጠ ሆኗል:: [13]

ቄሬኔዎስ በ7 B.C የሶርያ አገር ገዥ እንደ ነበረ በሥነ-ቅርስ ጥናት ሲረጋገጥ ጆሲፈስ የሚባለው አይሁዳዊ ታሪክ ጸሐፊ በክርስቶስ ዘመን አካባቢ የነበረ ደግሞ በ6 A.D ይኸው ቄሬኔዎስ አገረ ገዥ እንደ ነበረ ይገልጻል:: ስለዚህ በእነዚህ ዘመናት ቄሬኔዎስ የሶርያ አገረ ገዥ እንደነበረ ማስረጃ አለ ማለት ነው::

በተጨማሪም ሮማውያን በየ14 ዓመቱ የሕዝብ ቆጠራ ያደርጉ እንደ ነበረ በሥነ-ቅርስ ጥናት ተረጋግጦአል:: ይህንንም የሕዝብ ቆጠራ በሚያደርጉበት ገዜ በሥነ-ቅርስ ጥናት የተገኘ ጽሑፍ እንደሚያስረዳው ከቤታቸው ርቀው የሚገኙ ማናቸውም ሰዎች ወደ ቤታቸው ተመልሰው በአገራቸው በሕዝቡ ቆጠራ እንዲሳተፉ የሚያሳስብ ትእዛዝ ተገኝቶአል:: [14]

## ፲፬. የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ልዩነትና አንድነት

አስቀድመን እንደገለጽነው የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይና ማዕከላዊ መልዕክት፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሚገኘው ደኅንነት ስለሆነ የሁለቱ ኪዳኖች አንድነት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማተኮራቸው ነው።

## ልዩነታቸው

| | ብሉይ ኪዳን | አዲስ ኪዳን |
|---|---|---|
| ኢሳ. 9፣6-7 | 1. ኢየሱስ ክርስቶስ፤ መሲሑ ይመጣል | መሲሑ መጥቷል |
| ዕብ. 9፣12-14 | 2. የፍየሎች የበጎችና የኮርማዎች ደም ለኃጢአት ስርየት ይፈስ ነበረ | የእግዚአብሔር በግ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ፈሰሰልን |
| 2ቆሮ. 3፣3<br>ዕብ. 8፣10 | 3. በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፈ ሕግ | በልብ ጽላት ላይ የተጻፈ ሕግ |
| ዮሐ. 1፣17 | 4. የሕግ ዘመን | የጸጋ ዘመን |
| ዕብ. 10፣1 | 5. ጥላና ምሳሌ ነው | እውነተኛው አካል ነው |
| ዕብ. 9፣12፤25<br>ዕብ. 10፣3፤11-12 | 6. የደም መስዋዕት በየጊዜው ይቀርብ ነበር | ኢየሱስ አንድ ጊዜ ደሙን አፈሰሰልን |
| ዕብ. 7፣23-28 | 7. ብዙ ሊቀካህናት ነበሩ | አንድ ሊቀካህን አለን (ኢየሱስ) |
| ገላ. 3፣23-26<br>ዮሐ. 1፣12 | 8. እምነት እስኪመጣ ሕግ ሞግዚት ነበረ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንጂ ልጆች አልነበሩም | በክርስቶስ በማመን የሚገኝ ጽድቅና ልጅነት |
| 1ሳሙ. 16-13<br>ሐዋ. 2፣17፤ 5፣32 | 9. መንፈስ ቅዱስ በነሥታት፣ በነቢያት እና በካህናት ላይ ብቻ ይወርዳል | መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ላይ ይወርዳል |

# ዋቤ መጻሕፍት (Bibleography)

1. Unger, Merrill F. Survey of the Bible. (Harverst House publisher 1974) page 6
2. Geister, Norman L. and William E Nix. A General Introduction the Bible, revised and expanded Chicago: MOODY PRESS, 1986 Page 222-231
3. Ibid-Pages 232-233
4. McDowell, Josh, Ebidence that Demands a Verdict volume1. Here's Life publishers, Inc. 1989. page 30
5. Ibid-page 20
6. Ibid-page 20
7. Unger, Merrill F. The New Unger's Bible Dictionary. revised and updated edition, Chicago: Moody press. 1988. page 520
8. McDowell. Josh. Evidence that Demands a verdict volume1. Here's Life publishers. Inc 1989.-page 39
9. Ibid-page 57
10. Earle, Ralph. How We got our Bible. Grand rapids: baker book book house 1971. pages 48-49
11. Mcdowell. Josh. Evidence that demands a verdict volume Here's life publishers. Inc. 1989-page 55
12. Unger. Merrill F, The New Unger's Bible Dictionary. revised and udated edition, Chicago: Moody press, 1988. page 330
13. Mc Dowell. Josh, Evidence that Demadns a verdict volume Here's life publishers. Inc. 1989.-page 71
14. Ibid

# ምዕራፍ አንድ፣ ጥያቄዎች

1. ከእግዚአብሔር ቃል ባሕርያት ሦስቱን አብራራ፡
2. በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ስንት ስንት መጻሕፍት ይገኛሉ?
3. ብሉይ ኪዳን በስንት አቢይ ክፍሎች ይከፈላል? ምን ምን ናቸው? በእነዚያ ክፍሎችስ ስንት ስንት መጻሕፍት አሉ?
4. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው መጽሐፍ በተጻፉባቸው ጊዜያት መካከል ስንት ዓመታት አሉ መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ሰዎች ተጻፈ?
5. ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፉባቸውን ቋንቋዎች ጥቀስ፡፡
6. የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ መልዕክት ምንድነው? ማዕከላዊ ግለሰብ ማነው?
7. የእግዚአብሔር ሰዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት ለማካተት የተጠቀሙባቸው መመሪያዎች ምን ምን ናቸው? አዲስ ኪዳንን ለማካተት በተጨማሪ ምን መሟላት ነበረበት?
8. ከመንፈሳዊ መልዕክቱ ውጪ፤ እንደ አንድ የታሪክ መጽሐፍ ከሌሎች የታሪክ መጻሕፍት ጋር ሲወዳደር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማማኝነት ምን ትረዳለህ?
9. በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ግለጽ፡፡

# አምስቱን መጻሕፍት ከጊዜ አንጻር ስንመለከት

| ዘፍጥረት | ዘጸአት | ዘሌዋውያን | ዘኍልቁ | ዘዳግም |
|---|---|---|---|---|
| ከአዳም እስከ ዮሴፍ | ከዮሴፍ ሞት እስከ ከግብጽ ባርነት ወጥተው ሁለት ዓመት ድረስ | ከሁለተኛው ዓመት መጀመሪያው ወር እስከ ሁለተኛው ወር ዘኍ.1፣1) | ከግብጽ ከወጡ ከ2 ዓመት ጀምሮ 40 ዓመት እስኪያልቅ | ከ40ኛው ዓመት 11ኛው ወር እስከ 40ኛው ዓመት መጨረሻ |
| ከ2000 ዓመታት በላይ | ከ400 ዓመት በላይ ዘጸ. 40፣17 ሐዋ 7፣6 | የ1ወር ጊዜ | 38 ዓመታት | 1ወር + 1ወር ለሙሴ ለቅሶ = 2ወር ዘዳ. 1፣3-4 |